# መግቢያ

ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማዮሁ* በጥቅምት ወር 1992 ዓመት ምሕረት የዕድሜ ባለጸጋ ሁነው 90ኛ የልደት በዓላቸውን እንዳከበሩ ይታወሳል። ምንም እንኳን ሐሳቡ ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የተጸነሰ ቢሆንም፥ በጊዜና በእቅድ አለመገጣጠም ምክንያት ነገሩ በሁለት ወር ያህል ዘግይቶ፥ ታኅሣሥ 1 ቀን፥ 1992 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአራት ክፍሎች ተባባሪነት የኒህን "እውቅ" የሚል ቃል የሚያንሳቸውን ታላቅ ደራሲ የልደት በዓል ለማክበር አንዲት መለስተኛ መድበል በማሳተም አንድ ትሑት ዝግጅት በዩኒቨርሲቲው የድኅረ ምረቃ ጥናት ተቋም አዳራሽ ተደርጎ ነበር።

በዝግጅቱ የተባበሩት የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፥ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፥ የምርምርና የኅትመት ክፍል እና የውጭ ግንኙነት ክፍል ነበሩ። መድበሏን ተዘጋጅታ ለፍጻሜ እንድትደርስ ያበቋት የተለያዩ ግለሰቦች ቢሆኑም፥ የታኅሣሥ 1 1992ቱን ዝግጅት በማቀናበርና በመምራት በቀደምትነት ለተሰለፉትና ለዝግጅቱም ጽሑፍ ላቀረቡት ለዶክተር ፈቃደ አዘዘ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው፥ ለአቶ አስፋው ዳምጤ፥ ለአቶ ሺፈራው በቀለ፥ ለአቶ ብርሃኑ ገበየሁ፥ ለዶክተር ዮናስ አድማሱ በመጽሔታችን ስም ከፍተኛ ምሥጋና ልናቀርብ እንወዳለን።

ዝግጅቱ በተካሄደበት ወቅት፥ የዝግጅቱ አነሳሾች የነበራቸው የዘለቄታ ሐሳብ፥ *ለሀዲስ!!! 90ኛ የልደት በዓል* በሚል ርእስ በወቅቱ ታትማ በወጣችው፥ መድበል ውስጥ የወጡት አጫጭር ጽሑፎች ተስፋፍተውና በወጉ ተሟልተው በ*የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ ጽሑፍ መጽሔት* ልዩ እትም እንዲወጡ ማድረግ ነበር። ይህች የመጽሔታችን ልዩ እትም ይህንኑ ሐሳብ እውን ለማድረግ የተዘጋጀች ናት። እንደፕሮግራሙና እንደዚች መጽሔት አዘጋጆችም ሐሳብ፥ ይህች እትም ልትወጣ ከታሰበችበት ጊዜ በአንድ ዓመት ያህል ዘግይታለች። ለዚህ አያሌ የተወሳሰቡ ምክንያቶች ቢኖሩም፥ አንባቢዎቻችንን፥ ሐሳቡን የጸነሱትንና የታኅሣሡን ፕሮግራም ያዘጋጁትን፥ በተለይ ግን፥ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ይህ ነው የማይባል አስተዋጽኦ ያደረጉትንና ውለታቸው በምንም ዐይነት ተመን ሊተመን የማይችለውን ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማዮሁን ይቅርታ እንጠይቃለን።

---

* *ስማቸውን በመጀመሪያው የፍቅር እስከ መቃብር እትም* (1958) ላይ እንዳለው ማውጣታችን የደራሲውን ምርጫ ለማክበርና ስለአማርኛ ፊደል መሻሻል ያደረጉትንም ጥረት ለማስታወስና በመዘክርነት እንዲቆይ ለማድረግ ነው።

የሀዲስ አለማየሁን ልብ ወለድ ድርሰቶችና ሌሎች ሥራዎች፥ እንኳን በዚች ዐርበ ጠባብ መጽሔት ቀርቶ፥ በደረሷቸውና ለሕዝብ ባበረከቷቸው ጽሑፎች የገጽ ብዛት ልክ መርምሮ ያላቸውን ሰፊና እምቅ አንድምታ ለማሳየት ይቻላል የሚል እምነት የለንም። ገና መቼ ተነኩና! ገና መቼ በውል ተረዳናቸውና! የኛ ነገር መቼም፥ አለመታደልም ሊሆን ይችላል፥ "ነቢይ በሀገሩ አይከበርም" ሆነና፥ ለኒህ፥ ገና ከወጣትነታቸው ጀምሮ በረጋ ሥልት ማሰብ ለሚችሉ በሳል ደራሲ፥ ዲፕሎማት፥ እና መምህር የሚገባቸው ክብር በወጉ ደርሷቸዋል ብለን በድፍረት መናገር አንችልም። ቀደም ሲል፥ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት ተሸላሚ ሁነዋል፤ አሁን በቅርቡ (1992) የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በመስጠት አክብሯቸዋል። ይህ ሁሉ ይበል የሚያሰኝ ነው። ለሀዲስ፥ ትልቅ ክብርና ደስታ ይሆናቸዋል ብለን የምናምነው ግን፥ ሰው "የደገሰውን ቢበሉለት፥ የወለደውን ቢስሙለት" ነውና፥ የእርሳቸው የአእምሮና የምናብ ልጆች የሆኑትን ድርሰቶቻቸውን በጥሞና መርምሮ፥ አንድምታና ቁም ነገሮቻቸውን አንጥሮ ላለው ትውልድ መናኘት፥ ለመጪውም ማስተላለፉን ነው። የውጭ ደራስያን ለሰው ልጅ ባበረከቱት የአእምሮና የልቡና ምርት የሚገባቸውን ክብርና ምሥጋና ሳይከለከሉ፥ እስቲ እኒህን ታላቅ ሰውና ደራሲ መነሻ አድርገን፥ ሀገሪቱ፥ በየባህሉ፥ በየቋንቋው፥ በየመስኩ ያላጣቻቸውን ጥቂት የማይባሉ አሳቢዎች፥ ተመራማሪዎች፥ ደራሲዎችና መምህራን የሚገባቸውን ክብርና ትውስት እንንፈጋቸው ብለን በዚህ አጋጣሚ ልንማጸን እንወዳለን። የዚችም ልዩ እትም ትሑት ዓላማ፥ እንዲህ ያለውን ቅርስ ለመኮትኮትና ለማዳበር የሚቻልበትን ትልም እንተልም ብሎ ማሳሰብም ነው።

በመጨረሻም፥ ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ይህችን ትሑት አምኃችንን ይቀበሉን ዘንድ በታላቅ ትሕትናና አክብሮት እንጠይቃለን።

አዘጋጆቹ
1993 ዓ.ም.

---

ማስታወሻ፤ በሥራ ብዛትና በጊዜ ማነስ የተነሣ፥ ቀደም ሲል ለዘጠናኛ የልደት በዓላቸው ክብር ከተዘጋጁትና ተለቅመው ከቀረቡት የጽሑፍ መድበሎች አራቱ ብቻ ናቸው በዚች ልዩ እትም የቀረቡት።